የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ የካቲት ፫ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 13
ADDIS ABABA 10th February 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፺፫/፪ሺ፫

የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ......................ገጽ ፭ሺ፮፻፺፯

## CONTENTS

Regulation No. 193/2010

Ethiopian Standards Agency Establishment Council of Ministers Regulation ..........................Page 5697

<u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፫/፪ሺ፫</u>

## የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና ፴፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፫/፪ሺ፫ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ "ጥራት" ማለት በቀጥታ የተገለጸንና በተዘዋዋሪ መንገድ የተመለከተን ፍላጎት የማሟላት ችሎታውን የሚገልጽ የአንድ ምርት ወይም አገልግሎት አጠቃላይ ባሕሪ ነው፤

፪/ "ጥራት ማስፋፋት" ማለት በየደረጃው በሚገኙ የምርትና አገልግሎት ሂደቶች ላይ በተመጣጠነ የሀብት አጠቃቀም የጥራት ተፈላጊ ሁኔታዎችንና አላማዎችን በማሟላት የአንድን የአሰራር ሥርዓትና የአመራረት ብቃት ለማሳደግና ለማሻሻል የሚደረግ ማንኛውም እንቅስቃሴ ነው፤

<u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 193/2010</u>

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN STANDARDS AGENCY

This Regulation is issued by the Council of Ministers in accordance with Article 5 and 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010.

## PART ONE

## GENERAL

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Standards Agency Establishment Council of Ministers Regulation No. 193/2010".

**2. Definitions**

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "quality" means the general characteristics of products or services which describe the level of fulfillment of those direct and indirect requirements;

2/ "quality promotion" means any activity performed to improve the productivity and management system of each stage of product and service through the required quality objectives and conditions at optimum resource utilization;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4.70

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O. Box 80,001

፫/ "ደረጃ" ማለት ለጋራና ተደጋጋሚ ጥቅም መሟላት ያለባቸው ህጎች፣ መመሪያዎች ወይም የምርት ባህሪያትን እና ተዛማጅ ሂደቶችን ወይም የማምረቻ ዘዴዎችን የሚያስቀምጥ በጋራ መግባባት ላይ ተመሥርቶ ዕውቅና ባለው አካል የተዘጋጀ ሰነድ ሆኖ የአስተሻሸግና የመለያ ምልክት አደራረግ መስፈርቶችን ያጠቃልላል፤

፬/ "አስገዳጅ ደረጃ" ማለት ምርቶችና አገልግሎቶች የግድ ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶች የያዘ ደረጃ ነው፤

፭/ "የኢትዮጵያ ደረጃ" ማለት ማንኛውም ኤጀንሲው በብሔራዊ የኢትዮጵያ ደረጃነት አፅድቆ የሚያሳውቀው ደረጃ ነው፤

፮/ "ብሄራዊ የደረጃዎች ምልክት" ማለት ምርቶች አግባብነት ካላቸው የኢትዮጵያ ደረጃዎች ጋር መስማማታቸውን ለማረጋገጥ የሚያገለግል የብቃት ማረጋገጫ ምልክት ነው፤

፯/ "ምርት" ማለት ማናቸውም የኢንዱስትሪ ወይም የግብርና ውጤት ነው፤

፰/ "አገልግሎት" ማለት ለተጠቃሚው ጥቅም ሲባል በተጠቃሚው ጥያቄ በዋነኛነት በክፍያ የሚከናወን ማናቸውም ሥራ ነው፤

፱ "የገበያ ክትትል" ማለት ለገበያ የቀረበ ምርት ወይም አገልግሎት ተገቢውን የደረጃ መስፈርት ስለማሟላቱ ለማረጋገጥ የሚደረግ የቁጥጥር ስራ ነው፤

፲/ "ማሳወቅ" ማለት በህትመት ውጤቶች፣ በኤሌክትሮኒክስ መንገድ፣ በምስል ወይም በሌላ መገናኛ ዘዴ ለሚመለከታቸው አካላት ደረጃን ይፋ ማድረግ ነው፤

፲፩/ "የተስማሚነት ምዘና" ማለት ምርትን፣ አገልግሎትን ወይም የሥራ አመራር ሥርዓትን የሚመለከቱ ደረጃዎችና ሕግዊ መስፈርቶች መሟላታቸውን የማረጋገጥ ሂደት ነው፤

፲፪/ "የተስማሚነት ምዘና አካል" ማለት የሠርተፊኬሽን፣ የኢንስፔክሽን ወይም የላቦራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት የሚሰጥ አካል ነው፤

፲፫/ "የሥራ አመራር ሥርዓት" ማለት ጥራትን ለመጠበቅና አንድን ድርጅት ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ነው፤

፲፬/ "ብሄራዊ የጥራት መሠረተ ልማት" ማለት በደረጃዎች ዘርፍ፣ በሜትሮሎጂ ዘርፍ፣ በተስማሚነት ምዘና እና በአክሬዲቴሽን ዘርፍ የተዘረጋ የአሠራር ሥርዓት ነው፤

፲፭/ "ሠርተፊኬሽን" ማለት በተስማሚነት ምዘና ውጤት ላይ ተመሥርቶ የሚሰጥ ምስክርነት ነው፤

፲፮/ "ኢንስፔክሽን" ማለት የምርት ንድፍ፣ ምርት፣ ሂደት፣ አገልግሎት ወይም የተከላ ስራ ከዝርዝር መስፈርቶች በሙያዊ ምዘና ከሆነ ደግሞ ከጠቅላላ መስፈርቶች ጋር መስማማታቸውን

3/ "standard" means a document, developed by a recognized body on the basis of consensus, that provides, for common and repeated use, rules, guidelines or characteristics for products and their related processes or production methods and includes packaging and labelling requirements;

4/ "mandatory standard" means standard requirements that shall be fulfilled by products and services;

5/ "Ethiopian standard" means any standard approved and announced by the Agency as a national Ethiopian standard;

6/ "national standard mark" means a mark given for the substantiation that a product meets the requirements of the relevant Ethiopian standard;

7/ "product" means any industrially manufactured or agricultural product;

8/ "service" means any work done for or to the benefit of, and at the request of a recipient of services and normally provided for remuneration;

9/ "market surveillance" means a regulatory activity to check whether products or services supplied to the market meet the relevant standard requirements;

10/ "publicize" means making standards available by means of printing, electronic, photographic or any other medium to those concerned bodies;

11/ "conformity assessment" means a process of assuring that specified standards and legal requirements relating to product, service or management system are complied with;

12/ "conformity assessment body" means a body that delivers certification, inspection or laboratory testing service;

13/ "management system" means a process employed for attaining quality and productivity of an organization;

14/ "national quality infrastructure" means a system established for standardization, metrology, conformity assessment and accreditation;

15/ "certification" means a process of certifying on the basis of conformity assessment findings;

16/ "inspection" means examination of a product design, product, process, service or installation and determination of its conformity with specific requirements or, on the basis of professional judgement with

፲፯/ "የላቦራቶሪ ፍተሻ" ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተስማሚነት ምዘና ባህሪያት መሟላት አለመሟላታቸውን ለማረጋገጥ በግልጽ ተለይቶ የተወሰነ የምርመራ ሥርዓትን ተከትሎ የሚደረግ ምርመራ ነው፤

፲፰/ "አክሬዲቴሽን" ማለት የተስማሚነት ምዘና አካላት አስቀድሞ የተወሰኑ የብቃት መሥፈርቶችን መሟላታቸውን ለማረጋገጥ በሚካሄድ ግምገማ የሚሰጥ ምስክርነት ነው፤

፲፱/ "ሚኒስቴር" ማለት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነው፤

፳/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፳፩/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፪/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት
## የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ

### ፫. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

### ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

### ፭. ዓላማ

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ማዘጋጀትና ዕቃዎችና አገልግሎቶች ተፈላጊዎቹን ደረጃዎች አሟልተው መቅረባቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፤

፪/ ደረጃዎችን በመጠቀም የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ ሽግግር ማመቻቸት፤

፫/ ለሀገር በቀል ምርቶችና አገልግሎቶች ብሄራዊ ደረጃዎችን በማዘጋጀት በዓለም ዓቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ።

17/ "laboratory testing" means a test on whether or not one or more conformity assessment characteristics are in place through the use of specified test procedures;

18/ "accreditation" means evaluation and certification of conformity assessment bodies that they meet predefined competency requirements;

19/ "Ministry" means the Ministry of Science and Technology;

20/ "State" means any State referred to in Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

21/ "person" means any natural or juridical person;

22/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO
## THE ETHIOPIAN STANDARDS AGENCY

### 3. Establishment

1/ The Ethiopian Standards Agency (hereinafter the "Agency") is hereby established as an autonomous federal government office having its own legal personality.

2/ The Agency shall be accountable to Ministry.

### 4. Head Office

The Agency shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

### 5. Objectives

The Agency shall have the following objectives:

1/ to develop Ethiopian standards and establish a system that enable to check weather goods and services are in compliance with the required standards;

2/ to facilitate the country's technology transfer through the use of standards;

3/ to develop national standards for local products and services so as to make them competitive in the international market.

፮. <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ከሃገሪቱ የልማት መርሃ-ግብር ጋር የተጣጣመ የጥራት ማስፋፋት ተግባርን ለማከናወን የሚያስችል የደረጃ ዝግጅት ስትራቴጂ የማዘጋጀት፣ ተግባራዊ የማድረግና አፈፃፀሙን የመከታተል፤

፪/ የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የማዘጋጀት፣ የማጽደቅና የማሳወቅ፤

፫/ የደረጃዎች ሥራ በሚያከናውኑ ብሔራዊ፣ አህጉራዊ፣ ዓለም ዓቀፋዊ ወይም ሌሎች አካላት ለተዘጋጁ ደረጃዎች እንደየአስፈላጊነቱ እንደ ኢትዮጵያ ደረጃ ዕውቅና የመስጠት፤

፬/ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የሚያዘጋጁ ብሔራዊ የቴክኒክ ኮሚቴዎችን የመመስረትና የአሠራር መመሪያቸውን የመወሰን፤

፭/ ብሄራዊ የደረጃዎች ምልክትን ቅርጽና ይዘት የመወሰንና በምልክቱ የመጠቀም ፈቃድ የመስጠት፤

፮/ የደረጃዎች፣ የተስማሚነት ምዘና መመሪያዎችና የቴክኒክ ደንቦች ብሔራዊ መረጃ ማዕከል የማደራጀትና አገልግሎት የመስጠት፤

፯/ በተጠቃሚው ዘንድ የጥራትና የደረጃዎች ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶችን መንደፍና ተግባራዊ የማድረግ፤

፰/ ደረጃዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የቴክኒክ ድጋፎችን፣ ሥልጠናዎችንና የማማከር አገልግሎቶችን በመስጠት የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች የቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፤

፱/ ድርጅቶች የራሳቸውን ደረጃ የማዘጋጀት አቅም እንዲያዳብሩ የቴክኒክ ድጋፎችን፣ ሥልጠናዎችንና የማማከር አገልግሎቶችን የመስጠት፤

፲/ በምርት ሂደት ላይ ብክለትንና ብክነትን ለማስወገድ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም ልምድ በኢንዱስትሪዎች ውስጥ የማስፋፋት፤

፲፩/ የቴክኒክ ደንቦች አዘገጃጀት የዓለም ንግድ ህግጋት መስፈርቶችን የተከተለ እንዲሆን ለማስቻል ከሚመለከታቸው ብሔራዊና ዓለምአቀፍ ተቋማት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን የመመስረት፤

፲፪/ ብሔራዊ የጥራት ሽልማት ሥርዓት ለመመሥረት የሚያስችል ጥናት የማካሄድና ሲፈቀድም የማስተዳደር፤

፲፫/ ደረጃዎችን በሚመለከት በዓለም ዓቀፍ መድረክ የሀገሪቱን ጥቅም መወከልና ሀገሪቱ ተዋዋይ ወገን የሆነችባቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊነት የመከታተል፤

፲፬/ ለብሔራዊ የጥራት መሰረተ ልማት መጠናከር የተቀናጀ ድጋፍ መኖሩን ለማረጋገጥ ተገቢነት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት

6. <u>**Powers and Duties**</u>

The Agency shall have the powers and duties to:

1/ develop, implement and follow up standardization strategy for the purpose of quality promotion activities which are in line with the country's developmental programs;

2/ develop, through stakeholders involvement, approve and publicize Ethiopian standards;

3/ recognize any standard published by a national, regional, international or any other standardization body as Ethiopian standard, as may be relevant;

4/ establish national technical committees for the purpose of developing Ethiopian standards and determine their working guidelines;

5/ determine the shape and content of the national standard mark and authorize its use;

6/ establish national enquiry point and deliver services on standardization, conformity assessment guidelines and technical regulations;

7/ develop and implement awareness creation strategies for consumers on quality and standards;

8/ enable domestic industries to benefit from technology transfers through providing technical support, training and consultancy services in the implementation of standards;

9/ build the capability of companies through technical support, training and consultancy services for developing their own company standards;

10/ promote the use of technologies, in the industries, which help to reduce polution and wastage during production process;

11/ work in collaboration with the concerned national and international institutions to ensure that technical regulations are developed in line with world trade legal requirements;

12/ undertake studies for the establishment of national quality award system and administer same upon approval;

13/ represent the country's interest in international forums regarding standards and follow up the implementation of treaties to which Ethiopia is a party;

14/ work in cooperation with the relevant stakeholders to ensure the existence of an integrated support for strengthening the national quality infrastructure;

፲፭/ በደረጃዎች ዝግጅት፣ አተገባበርና በሚያስከትሉት ተፅዕኖና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ምርምሮችን ማካሄድ፤

፲፮/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ዋጋ የማስከፈል፤

፲፯/ የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በራሱ ስም የመክሰስና የመከሰስ፤

፲፰/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

**፯. የኤጀንሲው አቋም**

ኤጀንሲው፡-

፩/ ብሔራዊ የደረጃዎች ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ)፣

፪/ በመንግስት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ እና

፫/ አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል፡፡

**፰. የምክር ቤቱ አባላት**

፩/ ምክር ቤቱ አግባብ ካላቸው መንግሥታዊና ሌሎች አካላት ተውጣጥተው በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፡፡

፪/ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የምክር ቤቱ አባልና ፀሐፊ ይሆናል፡፡

**፱. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ኤጀንሲው አዘጋጅቶ የሚያቀርባቸውን ብሔራዊ የጥራትና የደረጃዎች ስትራቴጂዎችን ያፀድቃል፤

፪/ ብሔራዊ የደረጃዎች ምልክትን በአስገዳጅነት መጠቀም የሚገባቸውን ምርቶች ይወስናል፤

፫/ በብሔራዊ የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተዘጋጅተው የሚቀርቡ አስገዳጅ የሆኑ ወይም ያልሆኑ የደረጃ መስፈርቶችን በመገምገም ያፀድቃል፤

፬/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ለሌሎች ደረጃዎች እንደ ኢትዮጵያ ደረጃ የሚሰጥ እውቅናን ያፀድቃል፤

፭/ ኤጀንሲው በዚህ ደንብ መሠረት የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ያፀድቃል፤

፮/ ለብሔራዊ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት የሚከፈለውን አበልና ኤጀንሲው ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚጠየቁ የክፍያ ተመኖችን ለመንግሥት አቅርቦ ያፀድቃል፤

፯/ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የዘርፍ አማካሪ

15/ undertake research on the development, application and impacts of standards and related issues;

16/ charge fees for the services it renders in accordance with the rate determined by the government;

17/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

18/ carry out other related activities necessary for the attainment of its objectives.

**7. Organization of the Agency**

The Agency shall have:

1/ a National Standardization Council (hereinafter the "Council",

2/ a Director General and, as may be necessary, a Deputy Director General to be appointed by the government, and

3/ the necessary staff.

**8. Members of the Council**

1/ Members of the Council shall be drawn form the appropriate government and other bodies and be designated by the government.

2/ The Director General of the Agency shall be member and secretary of the Council.

**9. Powers and Duties of the Council**

The Council shall have the powers and duties to:

1/ approve the national quality and standardization strategy proposed by the Agency;

2/ determine products for which use of the national standard mark shall be mandatory;

3/ examine and approve mandatory and optional standard requirements proposed by national technical committees;

4/ approve the recognition of other standards as Ethiopian standards pursuant to sub-article (3) of Article 6 of this Regulation;

5/ approve directives to be issued by the Agency pursuant to this Regulation;

6/ submit for approval of the government the allowances to be paid to national technical committee members and the rate of fees to be charged for the services of the Agency;

7/ establish sectoral advisory committees as may be

## ፲. የምክር ቤቱ ስብሰባ

፩/ ምክር ቤቱ ለሥራው ባስፈለገ መጠን ይሰበሰባል፡፡

፪/ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላቱ ከተገኙ ምልአተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ የምክር ቤቱ ውሳኔ የሚተላለፈው ከአባላቱ በአብዛኛው ድምፅ ሲደገፍ ይሆናል፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፩. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፯ የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኤጀንሲውን ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም እንደተፈለገው ሊገኙ የማይችሉ ባለሙያዎችን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኤጀንሲውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለኤጀንሲው በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ኤጀንሲው ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ) የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና ሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኤጀንሲው ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ፲፪. በጀት

የኤጀንሲው በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

## ፲፫. የሂሳብ መዛግብት

፩/ ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ

## 10. Meetings of the Council

1/ The Council shall meet as frequently as its functions require.

2/ There shall be a quorum when more than half of the members of the Council are present at any meeting.

3/ Decisions of the Council shall be made by majority votes; in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article the Council may adopt its own rules of procedure.

## 11. Powers and Duties of the Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Agency and shall direct and administer the activities of the Agency.

2/ Without limiting the generality stated under sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Agency specified under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees of the Agency in accordance with the federal civil service laws and, in the case of employees with rare skills, in accordance with directives approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;

c) prepare the work programs and budgets of the Agency and implement same upon approval;

d) effect expenditures in accordance with the approved budget for the Agency;

e) represent the Agency in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Agency.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officials and employees of the Agency to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Agency.

## 12. Budget

The Agency's budget shall be allocated by the government.

## 13. Books of Accounts

1/ The Agency shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Agency shall be audited annually by the Auditor General or by auditors designated by him

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፬. ብሔራዊ የደረጃዎች ምልክት

፩/ ለማንኛውም ምርት ብሔራዊ የደረጃዎች ምልክትን ለመጠቀም ምርቱ አግባብነት ካለው የኢትዮጵያ ደረጃ ጋር መስማማቱ ኃላፊነት በተሰጠው የተስማሚነት ምዘና አካል ተረጋግጦ በኤጀንሲው መፈቀድ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም በብሔራዊ የደረጃዎች ምልክት ለመጠቀም ፈቃድ የተሰጠው ሰው ምልክቱን መጠቀም የሚችለው ለተፈቀደለት ምርት ብቻ ነው፡፡

፫/ ኤጀንሲው የደረጃዎች ምልክት የመጠቀም ፈቃድ የተሰጣቸውን ሰዎች ዝርዝር ሁኔታ የሚያሳይ ለህዝብ ክፍት የሆነ መዝገብ ይይዛል፡፡

፬/ የፈቃድ ተጠቃሚው የተሰጠውን ፈቃድ በድርጅቱ ውስጥ በቀላሉ ሊታይ በሚችልበት ቦታና አኳኋን ማኖር አለበት፡፡

፭/ በብሔራዊ የደረጃዎች ምልክት የመጠቀም ፈቃድ የሚሰጥበት፣ የሚታደስበት፣ የሚታገድበትና የሚሰረዝበት ሁኔታ፣ የምልክቱ አጠቃቀም እንዲሁም ከእነዚሁ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት ሁኔታ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

### ፲፭. በሕግ አስፈፃሚ አካላት የሚወሰዱ እርምጃዎች

፩/ አግባብ ያላቸው የፌዴራልና የክልል ሕግ አስፈፃሚ አካላት የሚከተለው ሥልጣን በዚህ ደንብ ተሰጥቷቸዋል፡-

ሀ) ብሔራዊ የደረጃዎች ምልክትን መጠቀም ግዴታ የሆነባቸው ወይም አስገዳጅ የደረጃዎች መስፈርትን ማሟላት የሚገባቸው ምርቶች ብሔራዊ የደረጃዎች ምልክቱ ሳይደረግባቸው ወይም አስገዳጅ የደረጃዎች መስፈርቱን ለማሟላታቸው ማረጋገጫ ሳይቀርብላቸው ወደ ኢትዮጵያ ግዛት እንዳይገቡ ወይም ከኢትዮጵያ ግዛት እንዳይወጡ የመከልከል፤

ለ) የገበያ ክትትል በማድረግ ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶችና አገልግሎቶች አግባብነት ያላቸውን አስገዳጅ የደረጃ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን የመቆጣጠር፤

## PART THREE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 14. National Standard Mark

1/ The use of the national standard mark with respect to any product shall require the holding of a permit issued by the Agency upon ascertaining the conformity of the product to the relevant Ethiopian standard by an authorized conformity assessment body.

2/ Any person authorized to use the national standard mark shall use the mark only for those products specified in the permit.

3/ The Agency shall keep a register showing descriptions of persons authorized to use the national standard mark, and the register shall be open to the public.

4/ Any permit holder shall display his permit within his business premises at a conspicuous place and in such a manner that it shall be easily visible.

5/ The conditions of issuance, renewal, suspension and revocation of permits for the use of the national standard mark, the manner of its use, and grievance handling procedures in relation thereto shall be prescribed by directive to be issued by the Agency.

### 15. Measures to be Taken by Law Enforcement Bodies

1/ The relevant federal and regional law enforcement bodies are hereby given the powers:

a) to prohibit the import or export of products subject to mandatory use of the national standard mark or the fulfilment of mandatory standard requirements without the use of the national standard mark or the presentation of certification for the fulfilment of the mandatory standard requirements;

b) to undertake market surveillance and take control measures to ensure the conformity of products and services with the relevant mandatory standard requirements;

ሐ) አግባብነት ያላቸውን አስገዳጅ የደረጃ መስፈርቶች ባለማሟላታቸው የተያዙ ምርቶች አስፈላጊ ማስተካከያዎች ተደርገውባቸው እንደገና ለገበያ እንዲቀርቡ የመፍቀድ ወይም ሊስተካከሉ የማይችሉና በተጠቃሚው ጤንነት ወይም ደኅንነት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ሲሆኑ የሚወገዱበትን ሁኔታ የመወሰን፤ እና

መ) ለገበያ ባቀረቧቸው ሰዎች በተገለፀው ወይም የተስማሚነት ምዘና አካላት የጥራት ምልክት በሰጡበት የደረጃ መስፈርት መሠረት በገበያ ላይ የዋሉ ምርቶች በተባለው የደረጃ መስፈርት መሠረት ለገበያ ስለመቅረባቸው አስተማማኝ አገልግሎት በሚሰጡ የተስማሚነት ምዘና አካላት የማረጋገጥና ውጤቱን በመገናኛ ብዙሐን ለህዝብ የማሳወቅ፡፡

፪/ ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው የሕግ አስፈጻሚ አካላት በዚህ አንቀጽ የተሰጣቸውን ሥልጣን በሥራ ላይ በሚያውሉበት ወቅት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## ፲፮. ፀንተው የሚቆዩ ደንቦች

ከዚህ ደንብ ጋር የማይቃረኑ የደረጃዎች ማህተምና የአገልግሎት ዋጋ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፹፱ ድንጋጌዎች በአዲስ ደንብ እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

## ፲፯. መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ

ከሜትሮሎጂ ጋር ከተያያዙት በስተቀር የኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች እና የኢትዮጵያ ክሊነር ፕሮዳክሽን ማዕከል በመባል ይታወቅ የነበረው ተቋም መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኤጀንሲው ተላልፈዋል፡፡

## ፲፰. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፫ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

c) in the case of products seized due to their failure to conform with the relevant mandatory standard requirements, to authorize their re-introduction to the market after taking the necessary corrective measures or to decide the manner of their disposal where corrective measures are not possible and that they may entail a threat to the health or safety of consumers; and

d) to engage the services of reliable conformity assessment bodies to ascertain whether or not products and services available in the market conform to the standard requirements declared by their suppliers or to that of the quality marks of conformity assessment bodies they are using, and disclose the findings thereof to the public through the mass media.

2/ Any concerned person shall have the duty to cooperate with the law enforcement bodies in exercising their powers under this Article.

## 16. Effectiveness of Regulations

The provisions of the Standard Mark and Service Fee Council of Ministers Regulation No. 13/1990 shall, in so far as they are not inconsistent with this Regulation, continue in force until replaced by new regulations.

## 17. Transfer of Rights and Obligations

The rights and obligations of the Quality and Standard Authority of Ethiopia other than those relating to metrology and the rights and obligations of the body known as the Ethiopian Cleaner Production Centre are hereby transferred to the Agency.

## 18. Effective Date

This Regulation shall enter into force on up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 10[th] day of February, 2011.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA